# የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ ( ኢሕአፓ)

## Ethiopian People's Revolutionary Party (EPRP)

መጋቢት 22 ቀን 2004 ዓ.ም

## በአማራው ሕዝብ ላይ የተከፈተውን የማፈናቀል ዘመቻ ኢሕአፓ ያወግዛል

ከቤንቺ ማጂ አካባቢ ብዙ የአማራ ተወላጆች በኃይል ተፈናቅለው መውጣታቸው በቅርቡ እየተዘገበ ነው። ይህ በወያኔ ቆስቋሽነት እየተካሄደ ያለው ጸረ-አማራ ዘመቻ በጥብቅ መወገዝ ያለበት በመሆኑ ኢሕአፓ የመለስ ዜናዊን ጸረ ሕዝብ ቡድን በጥብቅ ያወግዛል።

ጫካ ገባሁ ሲል ጀምሮ ትግሌ ጸረ አማራ ነው ካለ ዘረኛ ቡድን ሌላ ባይጠበቅም ወያኔ የአማራውን ሕዝብ ለማጥፋት ገና ከደደቢት የጀመረውን ዘመቻ እያጧጧፈ መሆኑ እየታየ ነው። በቦታው ነዋሪ የሆነው ሕዝብ በነፃ ሃሳቡን ሳይሰጥበት የጎንደርና ወሎን መሬት ወደ ትግራይ ያጠቃለለው ወያኔ የአማራውን ሕዝብ ከለም መሬቶች አፈናቅሏል። የአማራ መሬት ያለውን የቋራን መሬትም ለሱዳን አስረክቧል ። በአርባጉጉ፣ በምስራቅ ወለጋ፣ በበደኖ፣ ... ወዘተም አያሌ አማሮችን ጨፍጭፏል ወይም አስገድሏል። ከቤንቺ ማጂ (ጉራ ፈርዳ) የተፈናቀሉት አማሮች ከሰሜን ሸዋ፣ መርሐቤቴ፣ ሞላሌ፣ መሀል ሜዳ፣ ዘመሮ፣ ... ወዘተ ወደ አካባቢው ከዓመታት በፊት የመጡና በሰላም ሲያርሱ የነበሩ ዜጎች መሆናቸው ታውቋል። እነዚህ በሰላም ከሚኖሩበት ተፈናቅለው፣ ተሳደው ወደ አዲስ አበባ የመጡት ዜጎች በቅድስት ማሪያም ቤተ ክርስቲያን ለመጠለል ቢሞክሩም በመከልከላቸው፤ ወደ መኢአድ ጽ/ቤት በመሄድ በዚያ ተጠልለው የሰነበቱ መሆኑ ይታወቃል። አሁን በመጨረሻ ግን የወያኔ ተቀጥያ የሆነው ብአዴን ካድሬዎቹን ልኮ ከመኢአድ ጽ/ቤት አውጥቶ ወዴት እንዳደረሳቸው አልታወቀም። ወያኔ በአማራው ሕዝብ በአጠቃላይና በተለይም የሸዋ አማራ በሚላቸው ላይ ያለው የከረረ ጥላቻ ደግሞ የታውቀና የተወገዘም ነው።

የወያኔ ጸረ አማራነት ካለው ጸረ ኢትዮጵያ አቅዋም ጋር የተያያዘ ቢሆንም ወያኔ አማራውን ለማድቀቅና ለመሰባበር ደግሞ ልዩ ትኩረት የሚስጥ መሆኑ ይታወቃል። ከአማራው ውጪ ስለ ኢትዮጵያ አንድነት የሚጨነቅ ሌላ ዜጋ የለም ብሎ ከሻዕቢያ ጋር ሆኖ ይጽፍ ይለፍፍ የነበረው ወያኔ አማራውን በማጥቃትና (በራሱ ቋንቋም እንደሚለው) በማምከን ጸረ ኢትዮጵያ ተልዕኮውን ከግብ የሚያደርስ ይመስለዋል።

ጸረ አማራው ዘመቻ ይከሽፋል !
ድል ለኢትዮጵያ ሕዝብ !!

EPRP
P.O.Box 73337
Washington DC, 20056
USA
Tel. 202-291-4217 Fax 202-291-7645

E-mail : ESPIC@aol.com
Website: www.EPRP.com

EPRP
BP 22
Bois colombes 92270
France